ሸሪዓዊ የምድር ቅጣት የተወሰነለትን ወንጀል የፈፀመና ቅጣቱም በዱንያ ተፈፃሚ የሆነበት ሰው አላህ በመጪውም አለም ባሪያውን በድጋሚ ከመቅጣት የላቀ ፍትሃዊ ነው።

ከዐሊይ ረዲየሏሁ ዐንሁ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- እንዲህ ብለዋል: "ሸሪዓዊ የምድር ቅጣት የተወሰነለትን ወንጀል የፈፀመና ቅጣቱም በዱንያ ተፈፃሚ የሆነበት ሰው አላህ በመጪውም አለም ባሪያውን በድጋሚ ከመቅጣት የላቀ ፍትሃዊ ነው። ሸሪዓዊ የምድር ቅጣት የተወሰነለትን ወንጀል የፈፀመ አላህም ለርሱ ምድር ላይ ሸሽጎለት ይቅር ካለው በኃላ አላህ ይቅር ያለውን አንዳች ነገር ወደ ኋላ ተመልሶ ከመቅጣትም የላቀ
እጅግ ቸር ነው።"
[ሐሰን ነው።] [ቲርሚዚና ኢብኑማጀህ ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- እንደዝሙትና ስርቆት የመሰሉ ሸሪዓዊ የምድር ቅጣቶችን የሚያስፈርዱ ወንጀሎችን የፈፀመ ሰውና ቅጣቱን በምድር መቅጫ ሸሪዓው ህግ መሰረት የተቀጣ ይህ መቀጣቱ የተቀጣባትን ወንጀል እንደሚያብስለት፤ በመጪው አለም ያለበትንም ቅጣት እንደሚያስነሳለት ተናገሩ። ምክንያቱንም ሲገልፁ አላህ በባሪያው ላይ ሁለት ቅጣቶችን ሰብስቦ ከመቅጣት የላቀ አዛኝና ቸር ነው አሉ። አላህ በዱንያ ወንጀሉን የሸሸገለት፤ በዛ ወንጀሉም ያልቀጣው፤ አላህ ይቅር ያለውና የማረው ሰውም አላህ ዐዘ ወጀል የማረውንና ይቅር ያለውን ወንጀል ወደ ኋላ ተመልሶ ከመቅጣትም የላቀ የተከበረና ቸር ነው አሉ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/66211